ጎዳር 2026፣
ለአሁኑ እና ወደፊት ለሚቀላቀሉ የአሌክሳንድሪያ ሲቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) ታይታን ቤተሰቦች በሙሉ ሰላምታ ይድረሳቹ፣
የ2026-27 የትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ሩብ ዓመትን አጠናቀን ለ2027-28 የትምህርት ዘመን የትምህርት ምክር (academic advising) ሂደት ለመጀመር ተዘጋጅተናል። ተማሪዎች በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ በኮርስ መረጣ ሂደት ውስጥ የሚረዳቸውን መረጃ ያገኛሉ። የአሌክሳንድሪያ ሲቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ACHS) የምክር አገልግሎት ክፍል (Counseling Department) ስለዚህ አስፈላጊ ሂደት ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ሲል ይህንን መረጃ ለቤተሰቦች አስቀድሞ ያካፍላል። ***ልጅዎ በዚህ ወሳኝ የትምህርት ጉዞ ወቅት ድጋፍ እንዲያገኝ የሚረዱ ጠቃሚ ዝርዝሮችን ሰለያዘ እባክዎ ይህንን ደብዳቤ ሙሉ በሙሉ እንዲያነቡት እናበረታታዎታለን።***

ሰኞ፣ ኖቬምበር 9 እና ኖቬምበር 16 ቀን 2026 ፣ የACHS መምህራን በምክር አገልግሎት ክፍሉ (Counseling Department) የተዘጋጀውን የመጀመሪያውን **የትምህርት ምክር (Academic Advising)** በአምስተኛው (የምክር/advisory) ክፍለ ጊዜ ያካፍላሉ። ተማሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር የሚጣጣሙ የሥራ መስኮችን እንዲያገኙ የሚረዳቸውን የ**AchieveWorks Skills** ምዘናዎች በNaviance ውስጥ አጠናቀዋል። ተማሪዎች ውጤታቸውን ከቢታቸው ሆነው ማየት የሚችሉ ሲሆን ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን ውጤቱን እንዲመለከቱ ይበረታታሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ኖኔምበር 23 ቀን 2026 የሚቀርበውን የ2027 የበይነመረብ (virtual) የትምህርት ምክር **አውደ ርዕይ** ገለጻ (Academic Advising fair presentation)፣ እንዲሁም ኖቬምበር 30 ቀን 2026፣ በምክር ክፍለ ጊዜ (advisory lesson) ወቅት የሚሰጠውን **የሥራ መስኮች ስብስብ** (Career Clusters) አጠቃላይ እይታ ያገኛሉ። ሁሉም የምክር ትምህርቶች በሁሉም ካምፓሶች ለሚገኙ ተማሪዎች **በTitan Student Resources Canvas** ገጽ ላይ ይገኛሉ። የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Middle school) ቤተሰቦች ስለ ምክር ትምህርቶች የተለየ መልዕክት የሚደርሳቸው ሲሆን፣ ለACHS ተማሪዎች የሚቀርቡ ገለጻዎች በሙሉ በቀጣይ ቀን ለስምንተኛ ክፍል ቤተሰቦች ይጋራሉ።

እባክዎ ከኖቬምበር 30 ቀን 2026 እስከ ጃንዋሪ 29 ቀን 2027 የሚገኙ ተጨማሪ ግብዓቶችን (resources) በተመለከተ መረጃ የያዘውን ዝርዝር **የዝግጅቶች የቀን መቁጠሪያ** (calendar of events) ለማየት ጊዜ ይውሰዱ፤ እንዲሁም በእያንዳንዱ አካዳሚ ውስጥ ያሉ ልዩ የትምህርት አማራጭ መንገዶችን ለማየት የ**Academies at Alexandria City ድረ-ገጽን** ይጎብኙ። ሁሉም ቤተሰቦች ከጃንዋሪ 6 እስከ ጃንዋሪ 29 ቀን 2027 ባለው ጊዜ ውስጥ የበይነመረብ መጠይቅ (online survey) በመጠቀም የሥራ መስክ ስብስብ (career cluster) ምርጫዎችን (አስፈላጊ ከሆነ) እና ቀዳሚ ሦስት የአካዳሚ ምርጫዎችን የማስገባት ዕድል ይኖራቸዋል። ሁሉንም ቀዳሚ ጥያቄዎች ለማስተናገድ በቂ ክፍት ቦታዎች ከሌሉን ለአካዳሚ ምርጫ የዕጣ አወጣጥ ሥርዓት እንጠቀማለን። ከዚህ የትምህርት ዘመን በኋላ የአካዳሚ ለውጥ ለማድረግ ሌላ ዕድል ለማይኖራቸው የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች (sophomores) ቅድሚያ ይሰጣል።

(የአካዳሚ/የትምህርት አማራጭ መንገዶች መረጣ)
የትምህርት ቤቱ አማካሪ በግል ወቅት ከልጅዎ ጋር ምርጫዎቹን ይገመግማል። ቤተሰቦች የአካዳሚ ምርጫዎችን ለማስተካከል እስከ ማርች 12 ቀን 2027፣ ድረስ የትምህርት ቤቱን አማካሪዎች ማግኘት ይችላሉ።

- **ስምንተኛ ክፍል፡-** የመጀመሪያ የአካዳሚ ምርጫዎችን ማድረግ (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ምርጫ)።
- **ዘጠነኛ ክፍል፡-** በተመረጠው አካዳሚ መቀጠል ወይም በትምህርት ምክር (academic advising) ወቅት መቀየር። በዚህ ደረጃ ለመቀየር የሚወስኑ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታቸው አካዳሚ የመቀየር **ብቸኛ** ዕድላቸውን ይጠቀማሉ።
- **አሥረኛ ክፍል፡-** በተመረጠው አካዳሚ መቀጠል ወይም በትምህርት ምክር ወቅት መቀየር። በዚህ ደረጃ ለመቀየር የሚወስኑ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታቸው አካዳሚ የመቀየር **ብቸኛ** ዕድላቸውን ይጠቀማሉ።
    - **እባክዎ ይህን ልብ ይበሉ፡-** ለዚህ የትምህርት ዘመን አካዳሚዎን የመቀየር ብቸኛ ዕድልዎን ተጠቅመው ከነበረ፣ ሌላ የአካዳሚ ለውጥ ማድረግ አይችሉም፤ ስለዚህ ከ8ኛ እስከ 10ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የሚላከውን የአካዳሚ/የትምህርት መንገድ መጠይቅ (Academy/Pathway survey) መሙላት አይኖርቦትም።
- **አሥራ አንደኛ ክፍል፡-** ሁሉም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች (juniors) በዚህ ደረጃ በአካዳሚያቸው ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ ማድረግ አይፈቀድላቸውም።

ሁሉም ተማሪዎች ከእነዚህ አራት (4) አካዳሚዎች በአንዱ ውስጥ የሚገኝ የትምህርት መንገድ (pathway) መምረጥ አለባቸው፡-

1. የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ (STEM) አካዳሚ
2. የንግድ እና የመንግሥት አስተዳደር አካዳሚ
3. የትምህርት፣ የሰብአዊ ጥናት እና የሰብአዊ አገልግሎቶች አካዳሚ ወይም
4. የሥነ-ጥበብ፣ የትወና እና የተግባር ጥበባት አካዳሚ።

በሊንተርናሽናል አካዳሚ እና በከተሞአቀፍ ፕሮግራም) የተመዘገቡ ተማሪዎች የአጠቃላይ ጥናቶች አካዳሚን (General Studies Academy) መምረጥ አለባቸው።
በተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታ ውስጥ የአካዳሚ ምርጫን እና የትምህርት ሙያ እቅድን አስቀድሞ ማዘጋጀት፣ ተማሪዎች የመጨረሻ ዓመታቸው (senior year) ላይ ከመድረሳቸው በፊት የምረቃ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ይረዳቸዋል፤ በትናንሽ የመማሪያ ማህበረሰቦች አማካኝነት የተማሪዎችን ተሳትፎ ያሳድጋል፤ እንዲሁም ተማሪዎች ለስኬታማ የወደፊት ሕይወት ጠንካራ መሠረት እየገነቡ በሚስባቸው መስክ እንዲማሩ እና የተማሩትን በተግባር እንዲያውሉ ዕድል ይሰጣል። ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በNaviance ውስጥ ከሚገኘው AchieveWorks የተገኙ ውጤቶችን፣ የአማካሪዎችን ትምህርቶች፣ የአካዳሚዎችን ድረ-ገጽ፣ የምሽት ፕሮግራሞችን እና የተማሪዎች የግል ስብሰባዎችን በመጠቀም በመረጃ ላይ የተመሠረተ የአካዳሚ ምርጫ ማድረግ ይችላሉ። የACHS የትምህርት ቤት አማካሪዎች ተማሪዎች እስካሁን ድረስ ያልወሰኑ ከሆነ የፍላጎት፣ የዝንባሌ፣ የተሰጥኦ እና የችሎታ መስኮቻቸውን እንዲያጠቡ ለመርዳት ይህንን መረጃ ይጠቀማሉ።

የአካዳሚ እና የትምህርት መንገድ (pathway) ምርጫው ተማሪዎች ወደፊት በማንኛውም የሥራ ዘርፍ ቢሰማሩ የሚጠቅሟቸውን እንደ የፈጠራ እና የጥልቅ አስተሳሰብ ችሎታዎች ያሉ ለተለያዩ መስኮች የሚያገለግሉ ክህሎቶችን (transferable skills) እንዲያዳብሩ እንደሚያግዛቸው እባክዎ ያስታውሱ። ተማሪዎች **የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የምረቃ መስፈርቶችን** ለማሟላት ሁለት **ተከታታይ ተመራጭ ትምህርቶችን (sequential electives)** መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት መንገዶች ውስጥ እነዚህን ተከታታይ ተመራጭ ትምህርቶች የመምረጥ ዕድል ይኖራቸዋል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ ስለ **አካዳሚዎቹ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን** የያዘውን ሰነድ ይመልከቱ።

የትምህርት ምክር የአንድ ለአንድ ውይይቶች

በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ተማሪዎች ሰባት (7) የትምህርት ዓይነቶችን መውሰዳቸውን ይቀጥላሉ። ቤተሰቦች ስለ ምርጫዎቹ የመወያየት እና የPowerSchool አካውንታቸውን በመጠቀም ምርጫዎቹን የማስገባት ዕድል ይኖራቸዋል። በተሻሻለው የ2027-2028 የትምህርት መርሃ-ግብር ላይ እንደተገለጸው፣ ተማሪዎች በየዓመቱ በአካዳሚያቸው ውስጥ አንድ ቀዳሚ ተመራጭ ትምህርት (primary elective) እና አንድ ተለዋጭ ትምህርት (alternate) መምረጥ ይኖርባቸዋል።
የትምህርት ቤት አማካሪዎች ተማሪዎችን በኮርስ መረጣ ሂደት ውስጥ የሚያግዙ ሲሆን፣ መጀመሪያ የተመረጡት ኮርሶች በተለያዩ የክፍለ ጊዜ መደራረብ ምክንያት የማይገኙ ከሆነ ሁለት (2) ተለዋጭ የተመራጭ ትምህርት አማራጮችን (alternate elective options) እንዲመርጡ ይጠይቃሉ። የኮርሶች ዝርዝር መግለጫ እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች በ**ACPS የትምህርት መርሃ-ግብር** ውስጥ ይገኛሉ። የተሻሻለው የ2027-28 የትምህርት መርሃ-ግብር እትም በጃንዋሪ 2027 ዝግጁ ይሆናል።

የሥራ መስክ እና የሥርዓተ-ትምህርት አውደ ርዕይ
ተማሪዎች በምክር ክፍለ ጊዜ ስለ ኮርሶቻችን የበለጠ ከመማራቸው በተጨማሪ፣ ሁሉም ቤተሰቦች ረቡዕ፣ **ዲሴምበር 9 ቀን 2026 ከምሽቱ 5:30 እስከ 8:00 ሰዓት (5:30–8:00 p.m.) በACHS ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King St. Campus)** በሚጀምረው ዓመታዊ የሥራ መስክ እና የሥርዓተ-ትምህርት አውደ ርዕይ (Career Pathway Curriculum Expo) ላይ እንዲገኙ ተጋብዘዋል። ይህ በአንድ ምሽት የሚካሄድ ጥምር ዝግጅት በአሌክሳንድሪያ ሲቲ የሚገኙ አካዳሚዎችን፣ የሥራ መስክ ትስስሮችን እና ሰፊ የትምህርት ዕድሎቻችንን የሚያስተዋውቅ ነው። ቀኑ ሲቃረብ የምሽቱን ዝግጅት ሙሉ መርሃ-ግብር እናካፍላለን፤ ለጊዜው ግን የምሽቱን ፕሮግራሞች አጭር ቅኝት ከዚህ በታች ቀርቧል፦

- ከመምህራን ጋር **ይገናኙ** እንዲሁም ስለ ዋና እና የአማራጭ የትምርህት ዓይነቶችን መረጃ የሚሰጡባቸውን ጠረጴዛዎች ጎብኙ።
- **ማቀድ ይጀምሩ** እንዲሁም በየክፍል ደረጃው በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ በሚቀጠለው ዓመት እንዲከናወኑ ስለ ሚጠበቁ ነገሮች ይወቁ።
- በመረጃ መስጫ ክፍለ-ጊዜዎች ላይ **ይገኙ** እና በአሌክሳንድሪያ ሲቲ አካዳሚዎች ውስጥ ስላሉት የትምህርት መንገድ (pathway) አማራጮች ይወቁ።
- የማህበረሰብ አጋሮቻችንን **ይተዋወቁ።**

በካምፓሶች መካከል ለሚደረግ ጉዞ የመጓጓዣ አውቶቡስ ይዘጋጃል።

የትምህርት ምክር ስብሰባዎች እና የኮርስ ምርጫ ማስተካከያዎች የጊዜ ሰሌዳ
ሂደቶችና መመርያዎች

የ2027-28 የትምህርት ዘመን የትምህርት ምክር ስብሰባዎች እና የኮርስ ምርጫ ማስተካከያዎች የጊዜ ሰሌዳ የሚከተለው ነው፦

- **ከጃንዋሪ 6–15 ቀን 2027፦** መምህራን በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር በመወያየት ለሚቀጥለው ዓመት ስላሉት የኮርስ አማራጮች ይመክራሉ፤ እንዲሁም ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ምርጫቸውን በPowerSchool ውስጥ ከማስገባታቸው በፊት እንዲያጤኗቸው የራሳቸውን የምክር ሀሳቦች ይሰጣሉ።
- **ከጃንዋሪ 19–25 ቀን 2027፦** መምህራን የሰጡትን የምክር ሀሳብ በPowerSchool ውስጥ ያስገባሉ።
- **ከጃንዋሪ 29–ፌብሯሪ 3 ቀን 2027፦** ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ምርጫዎቻቸውን በPowerSchool ውስጥ የማስገባት ዕድል ይኖራቸዋል። ምርጫዎቻችሁን በምታደርጉበት ወቅት የመምህራንን የምክር ሀሳብ ከግምት ውስጥ ማስገባታችሁን እባክዎ ያረጋግጡ። እባክዎ ስለ ትምህርት ምክር ሂደቱ ከልጆችዎ ጋር ለመነጋገር ጊዜ ይውሰዱ። ከፌብሯሪ እስከ ማርች ባለው ጊዜ ውስጥ የሚያደርጓቸው የኮርስ ምርጫዎች ለሚቀጥለው የትምህርት ዘመን የክፍል መርሃ-ግብር (schedule) ዝግጅት እጅግ ወሳኝ ናቸው። ተማሪዎች ከአማካሪያቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የተወሰነ ጊዜ ይኖራቸዋል። አማካሪዎች የክፍል መርሃ-ግብር እርማቶችን (schedule corrections) የሚያስተናግዱት በትምህርት ቤት የመጀመሪያ ሳምንት ብቻ በመሆኑ፣ በሂደቱ ላይ የተደረጉትን ለውጦች እባክዎ ልብ ይበሉ።
- **ከፌብሯሪ 8–ማርች 12 ቀን 2027** ተማሪዎች (ከ8ኛ እስከ ዘኛ ክፍል) በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ በተመረጡ የክፍለ ጊዜ ሰዓታት ከአማካሪዎቻቸው ጋር ይገናኛሉ። ተማሪዎች የአንድ ለአንድ የትምህርት ምክር ውይይታቸውን አስቀድመው አድርገው ከነበረ፣ የኮርስ ምርጫዎቻቸውን እና የአካዳሚ/የትምህርት መንገድ (academy/pathway) አማራጮቻቸውን ለማሻሻል ለትምህርት ቤት አማካሪያቸው ኢሜይል መላክ ይችላሉ።
- **የበይነመረብ (አንላይን) ኮርስ መረጣ፦** በየሴሚስተሩ ለበይነመረብ ኮርሶች ያሉት ክፍት ቦታዎች ውስን በመሆናቸው፣ በቅርቡ ለሚመረቁ ተማሪዎች እና በትምህርት ቤት የክፍለ ጊዜ መርሃ-ግብራቸው ምክንያት ትምህርቱን በአካል መውሰድ ለማይችሉ ተማሪዎች ቅድሚያ ይሰጣል። በተጨማሪም፣ የበይነመረብ ኮርሶች ተማሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር የሚጣጣሙ ነገር ግን በአካል የማይሰጡ ትምህርቶችን እንዲወስዱ ዕድል ይሰጣሉ። የበይነመረብ (አንላይን) ትምህርቶች ተማሪዎች የክፍል ሥራቸውን እንዲያጠናቅቁ የሚያስችሉ ቢሆንም፣ ትምህርቱን በወቅቱ ለመጨረስ ተማሪዎች የተቀመጠውን የትምህርት ፍጥነት (pace) መከተል እንዳለባቸው እባክዎ ልብ ይበሉ። በመሆኑም፣ የተማሪው የሩብ ዓመት ውጤት (በሩብ ዓመት ሪፖርት ካርድ ላይ የሚወጣው) የትምህርቱን የአጨራረስ ፍጥነት (pace) እና የትምህርት አቀባበል ብቃትን (performance) አጣምሮ በያዘ ቀመር የሚሰላ ነው። ተማሪዎች በሚጠበቀው ፍጥነት መጓዛቸው እጅግ ወሳኝ ነው። በመደበኛው የትምህርት ቀን ሰዓት (ከክፍለ ጊዜ 1–7 / blocks 1-7) የበይነመረብ ትምህርት የሚወስዱ ተማሪዎች ለበይነመረብ ትምህርት በተዘጋጀው መማሪያ ክፍል

ውስጥ መገኘት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ሰነድ ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ስለሚጠበቁ ግዴታዎች በዝርዝር ስለሚያብራራ፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በበይነመረብ ኮርስ ከመመዝገባቸው በፊት መሙላት ያለባቸውን የበይነመረብ ትምህርት ውል (Online Learning Contract) በደንብ ማንበብ አለባቸው።

- **ሜይ** 7 ቀን 2027፦ በተማሪዎች የምዝገባ ጥያቄዎች ብዛት ምክንያት ክፍት ወይም ዝግ በሆኑ ክፍሎች ላይ በመመሥረት ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው እንዲገመግሙ እና ማስተካከያ እንዲያደርጉ የኮርስ ምርጫዎቹ ይጋራሉ። የክፍል መርሃ-ግብር ማስተካከያዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው ከሜይ 7 እስከ ሜይ 28 ቀን 2027 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።
    - **ያስታውሱ (Remember): የአድቫንስድ ፕሌስመንት (AP) እና የዱዋል ኢንሮልመንት (DE) ኮርሶችን ጨምሮ፣ ከመምህራን የምክር ሀሳብ፣ አሁን ካለዎት ውጤት እና ከትምህርት ቤት ውጭ ጊዜ ከሚጠይቁ የግል ኃላፊነቶች ጋር በሚገባ የሚጣጣሙ ኮርሶችን መምረጥዎን እባክዎ ያረጋግጡ። የትምህርት ደረጃ ማስተካከያዎችን ማድረግ የሚችሉት በተወሰኑ የጊዜ ገደቦች ውስጥ ብቻ ይሆናል።**
    - ለመጪው (Fall 2027) ሴሚስተር የዱዋል ኢንሮልመንት (DE) ምዝገባ በሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ ያበቃል። ተማሪዎች ለDE ኮርሶች የትምህርት የመጀመሪያ ቀን ከመድረሱ በፊት መመዝገብ አለባቸው። ***ማሳሰቢያ፦ ተማሪዎች በክፍት ቦታ መኖር ላይ ብቻ በመመሥረት ወደ Honors ወይም AP ኮርስ ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ (level up) የሚጠይቁበት አንድ የመጨረሻ ዕድል ከአገስት 26–31 ቀን 2027) ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ይሰጣቸዋል።***
    - **<u>ተማሪዎች የጠየቋቸው ኮርሶች በሙሉ በትክክል መካተታቸውን ማረጋገጥ እና ማንኛውንም ማስተካከያ በዚህ ጊዜ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።</u>**
    - ተማሪዎች ሜይ 28 ቀን 2027 በኋላ ምንም ዓይነት ለውጥ መጠየቅ **አይችሉም**፤ ይህም የተመራጭ ትምህርት ዓይነቶችን (elective classes) ይጨምራል።
    - አንድ ተማሪ የመረጣቸውን ሰባት (7) ቀዳሚ ምርጫዎች ካገኘ፣ በፎል ወቅት (in the fall) ኮርሱን ወደ ተለዋጭ ክፍል (alternate class) አንቀይርም።
- **ሜይ 10 ቀን 2027፦** የተማሪዎች የአካዳሚ እና የትምህርት መንገድ (Academy/Pathway) ምደባ ለቤተሰቦች ይገለጻል።
- **ሜይ 28 ቀን 2027፦** የኮርስ ምርጫ ለውጦችን የሚገባበት የመጨረሻ ቀን።
- **ከአገስት 13–20 ቀን 2027፦** የትምህርት ቤት አማካሪዎች የሚጣረሱ የክፍለ ጊዜ መደራረቦችን (hard schedule conflicts) በተመለከተ ከቤተሰቦች ጋር በመገናኘት አማራጮችን ይሰጣሉ።
- **አገስት 18 ቀን 2027፦** የተማሪዎች የክፍል መርሃ-ግብር (schedules) በPowerSchool ውስጥ የሚለቀቅ ሲሆን ለቤተሰቦችም ክፍት ይሆናል። ለማስታወስ ያህል፣ የክፍል መርሃ-ግብር ለውጦች ተቀባይነት የሚኖራቸው **ከሜይ 7–28 ቀን 2027** ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው።
- **ከአገስት 23–27 ቀን 2027፦ ምዕራፍ 1** - የትምህርት ቤት አማካሪዎች በሚከተሉት ምድቦች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን የክፍል መርሃ-ግብር እርማቶችን (schedule corrections) **ብቻ** ለመፍታት ይደግፋሉ፦
    - እንደ አስፈላጊነቱ የኮርስ መደራረብን (course conflict) ለመፍታት የአቻ መካሪ (peer mentor) ወይም የቢሮ ረዳት (office aide) ክፍለ ጊዜ መጨመር።
        - *የአቻ መካሪ እና የቢሮ ረዳት ክፍለ ጊዜዎች በዋናነት በጸደይ ወቅት (spring) መመረጥ አለባቸው (ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ የሚፈቀድ ሲሆን፣ ተማሪዎቹም በወቅቱ ለመመረቅ በሚያስችል ሁኔታ ላይ መሆን አለባቸው)።*
    - በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ፈቃድ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ልዩ መብትን (Senior Privilege) ተግባራዊ ማድረግ
    - በክፍል መርሃ-ግብር ላይ የተደጋገመ ኮርስ ሲኖር
    - ዋና የትምህርት ዓይነት መጉደል
    - የምረቃ መስፈርት መጉደል
    - የክፍለ ጊዜ መጉደል
    - ለአንድ ኮርስ አስቀድሞ መወሰድ ያለበትን ወይም አብሮ መወሰድ ያለበትን ትምህርት አለመውሰድ
    - ከፌቡሯሪ 8 ቀን 2027 እስከ ሜይ 27 ቀን 2027 ባለው ጊዜ ውስጥ **ባልተመረጠ** የተመራጭ ትምህርት ዓይነት ውስጥ መመደብ (ክፍት ቦታ መኖር ላይ የተመሰረተ)
        - *የትምህርት ቤት አማካሪ እርማቱን ከማድረጉ በፊት ለማረጋገጥ ሰነዶችን ይገመግማል።*
    - ተማሪው (ቀድሞውኑ የትምህርት ነጥብ) ያገኘበትን የተደገመ ክፍል ማስወገድ
- የትምህርት ቤት አማካሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች **ማስተናገድ አይችሉም**፦
    - የመምህር ለውጥ
    - የተመራጭ ትምህርት ለውጥ
    - የክፍለ ጊዜ ለውጥ
    - የካምፓስ ለውጥ
- **ከአነስት 26–31 ቀን 2027፦** ተማሪዎች ክፍት ቦታ ካለ ወደ Honors ወይም AP ትምህርት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ (level up) መጠየቅ ይችላሉ።
    - ተማሪው ለከፍተኛ ደረጃ ኮርስ የሚያበቃውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ (እና ክፍት ቦታ ካለ) የትምህርት ጥንካሬን (academic rigor) ለመጨመር የክፍል መርሃ-ግብር ለውጦች ይፈቀዳሉ፦
        - በዋና የትምህርት ዓይነት ውስጥ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ኮርስ መዛወር (ለምሳሌ ከመደበኛ ሂሳብ ወደ Honors ሂሳብ መግባት)።
        - አስቀድመው መወሰድ ያለባቸውን ቅድመ-ሁኔታ ትምህርቶች (prerequisites) እስካጠናቀቁ ድረስ በከፍተኛ ደረጃ ተመራጭ ትምህርት ውስጥ መመዝገብ (ለምሳሌ Honors ወይም Advanced Placement ስፓኒሽ መጨመር)።

- *ልዩ ሁኔታ፦ ተማሪዎች የኖርዘርን ቨርጂኒያ ኮሚኒቲ ኮሌጅ (Northern Virginia Community College - NVCC) መስፈርትን ካላሟሉ፣ ወይም ትምህርቱን ማቋረጥ ከNVCC የትምህርት ማቋረጫ የጊዜ ገደቦች ጋር የሚጣጣም ከሆነ የዱዋል ኢንሮልመንት (dual enrollment) ኮርስን ማቋረጥ ይችላሉ።*
- *ልዩ ሁኔታ፦ ተማሪዎች የኖርዘርን ቨርጂኒያ ኮሚኒቲ ኮሌጅ (NVCC) መስፈርትን ካላሟሉ፣ ወይም በNVCC የኮርስ መሰረዣ የጊዜ ገደብ መሠረት ከሆነ፣ የDE ኮርስን መተው ይችላሉ።*
- *ተማሪዎች የመረጧቸው ሰባት (7) ቀዳሚ ምርጫዎች ከተመደቡላቸው፣ ወደ ተለዋጭ ምርጫዎቻቸው የመቀየር ዕድል እንደማይኖራቸው እባክዎ ልብ ይበሉ።*

- **ከሴፕተምበር 7–10 ቀን ፦ ምዕራፍ II** - ተማሪዎች ክፍት ቦታ እስካለ ድረስ ወደ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ለመውረድ ለሚመለከታቸው የአካዳሚ ርዕሰ መምህራን ጥያቄ የማቅረብ ዕድል ይኖራቸዋል። በዚህ ጊዜ የሚተዉ ትምህርቶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ሆነ በNOVA የውጤት መግለጫ (ለDE ኮርስ ተማሪዎች) ላይ አይመዘገቡም። ርዕሰ መምህራኑ የቀረበውን ጥያቄ በመገምገም በክፍል መገኘት (attendance)፣ በወቅታዊ የትምህርት ጥረት፣ ከመምህሩ እና ከቤተሰብ በሚሰጡ አስተያየቶች እንዲሁም በሌሎች ሁኔታዎች ላይ ተመሥርተው ውሳኔ ይሰጣሉ።
- **ከኦክቶበር 18–29 ቀን 2027፦ ምዕራፍ III (Phase III)** - ተማሪዎች ክፍት ቦታ እስካለ ድረስ ወደ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ለመውረድ ጥያቄ የማቅረብ ዕድል ይኖራቸዋል (የመምህሩ እና የአካዳሚው ርዕሰ መምህር ፊርማ ያስፈልጋል)። በዚህ ጊዜ የሚተዉ የDE ትምህርቶች በNVCC የውጤት መግለጫ (transcript) ላይ ይመዘገባሉ። ርዕሰ መምህራኑ የቀረበውን ጥያቄ በመገምገም በክፍል መገኘት፣ በወቅታዊ የትምህርት ጥረት፣ ከመምህሩ እና ከቤተሰብ በሚሰጡ አስተያየቶች እንዲሁም በሌሎች ሁኔታዎች ላይ ተመሥርተው ውሳኔ ይሰጣሉ።
- **ኖቬምበር 1 ቀን 2027እና ከዚያ በኋላ፦ ምዕራፍ IV** - ተማሪዎች እስከ 2ኛው ሩብ ዓመት (2nd quarter) መጨረሻ ድረስ ወደ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ መውረድ ይችላሉ፤ ነገር ግን ትምህርቱ በውጤት መግለጫው (transcript) ላይ ተመዝግቦ የሚቆይ ሲሆን፣ በማለፍ ያቋረጠ (Withdraw Pass - WP) ወይም በመውደቅ ያቋረጠ (Withdraw Fail - WF**)** የሚል ምልክት ይኖረዋል። ለምረቃ የግድ አስፈላጊ ያልሆነን ትምህርት **በማለፍ ያቋረጠ (WP)** ወይም **በመውደቅ ያቋረጠ (WF)** በሚል ምልክት የመተው ዕድል የሚኖራቸው የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች (Seniors) ብቻ ናቸው።

ስለ ትምህርት ምክር ሂደቱ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ተጨማሪ መመሪያ ከፈለጉ፣ የልጅዎን የACHS የትምህርት ቤት አማካሪ ወይም የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪ ለማነጋገር አያመንቱ።

አመሰግናለሁ፣

R. Briana Hardaway, Ed.S.
ACHS Director of High School Counseling